# <u>ሞት አይቀርም ተነስ።</u>

በቅርቡ የወያኔ ታጋይ የነበሩ የትግራይ ፖሊስ የኪነት ጓዶች ለፕሮፓጋንዳ ጎረቤት አገር ወደ ሆነቺው ወደ  ሱዳን ለፖለቲካ ቅስቀሳ በመሄድ ላይ እያሉ በመኪና አደጋ ምክንያት ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ለመሆናቸው በብሔራዊ ደረጃና የየክልሉ ባንዲራ ዝቅ ተደርጎ በመሰቀል በጥልቅ ሐዘን የተከበረና ለወያኔ ታጋይነታቸውም መታሰቢያ ሐውልት እየተሠራላቸው ሳለ የወያኔን ሥራ ደጋፊ የሆነ ሁሉ ኢትዮጵያ በመሄድ ለቅሶ መድረስና በወያኔያዊነት  የአቋም ድጋፍ መስጠት ሲችል፣ የተገላቢጦሽ ወያኔ ለሐዘኑ ቪዛ በመስጠት ወደ ባሕር ማዶ በመላክ በአሜሪካን ከተሞች ፍትሐት እንዲደረግላቸውና በውጭ አገር ያለን ኢትዮጵያውያን ሐዘን እንድንቀመጥና ገንዘብ መዋጮ ዲያስፖራው እንዲያደርግ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ ነው። ወያኔ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ድጋፍን ለማሰባሰብ የሚያደርገው ጥረት ባይደንቀንም፤ በመኪና አደጋውም ሆነ በራሱ በአጋዚ ጥይት በየጊዜው እየተገደሉ ያሉ ኢትዮያውያን ሁሉ እግዚአብሔር ነፍሳቸውን ይማርልን እንላለን።

በኢትዮጵያ በውሸት የአሸባሪነት ፖለቲካ ስም በእስር ቤት እየማቀቁ በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ላይ የሚያደረገውን ግፍና ሰቆቃ ማጠናከሪያ እውነት ለማስመሰል ድጋፍ ማግኘት የሚቻለው በውጭ አገር በስደት ላይ ያሉ የተደራጁ ማኅበረሰቦች፣ የተለያዩ ተቋማትንና በስደት የሚገኘውን ሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ ሥር የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት የአመራር አካላት ውስጥ ሰርጎ በመግባትና በመከፋፈል ተለጣፊ ወያኔያዊ ቡድን ለመፍጠር የሰለጠኑ የወያኔ ካድሬዎችን በውጭ አገር ካሰማራ ዓመታት አልፎታል። ይህንንም እኩይ ተልዕኮ ተግባራዊ እያደረጉ ይገኛሉ። ለዚህም ተግባር ወያኔ በአውሮፓ፣ በአሜሪካና በተለያዩ አገሮች ኢትዮጵያውያን በሚኖሩበት ቦታ ሁሉ የፕሮፓጋንዳ ሚዲያዎችን ለመቆጣጠር በሆዳም ደጋፊዎቹ በኩል ገንዘብ እያፈሰሰ ነው። ለምሳሌም የወያኔ ፕሮፓጋንዳ ሚዲያዎች ማለትም ቲቪና ሬዲዮ ጣቢያዎች፣ ድህረ -ገጾችና ፖልቶኮች ብዛት  መጥቀስ ይቻላል።

በፖለቲካ ችግሮች ወያኔን ማውገዙ ብቻ በቂ ስላልሆነ በድክመታችን መወቀስ ሆነ መታረም ያለበት ብዙ ነገሮች አሉ። ወያኔ አንድነታችንን እያናጋ ነው። ከዚህ አደጋ አገሬን ለማዳን እኔ ለአገሬ አንድነት ምን ሠራሁ? ብለን እራሳችንን እንጠይቅ፤ አገር ከእናት፣ ከአባትም ከሁልም በላይ መሆንዋ፤ እትብታችን ከምድሯ በመቀበሩ ከደማችንና ከሥጋችን ጋር ተቀላቅላለች። የስሜን አፍሪካ ሆነ የመካከለኛው ምሥራቅ ሕዝባዊ ንቅናቄዎች የተጀመረው በህዝባዊ አመጽ እንጂ መሣሪያን በመማዘዝ አይደለም። ታዲያ ኢትዮጵያ አገራችን የአረብ ልጆችን ያህል ልብ ያላቸው ጅግና ልጆች አልወለደችም ይሆን? ወይስ ወያኔው አፄ መለስ ዲክታተር አይደለም ማለት ነው?  ምነው ነጻነት ናፋቂ ወኔ ያለው እንዴት ከኢትዮጵያ ምድር ይጥፋ? የወያኔ ሰላይ ከህዝቡ ውስጥ እንደአሸን መፍላቱ ይሆን ትግሉን ያዳፈነው? ወይንስ እንደ ሰው በቀን ሦስት ጊዜ በልተን ጠግበን እየኖርን ይሆን ስለ መብታችን የማንከራከረው? ወይስ ከባርነት የማይሻለውን የወያኔ ሥርዓት ወደን ነው? የመሣሪያ ብዛት የነፃነት እንቅስቃሴዎችን አዳፍኖ የሚጨርስ ቢሆን ኖሮ የዛሬዋ ደቡብ አፍሪካ ነፃ ባልወጣችም ነበር፡፡ በሰሜን አፍሪካ በተለይም በግብጽ የለውጥ ብርሃን ጮራ ባልፈነጠቀም ነበር።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! እንደ ሌላው አገር እራስህን ታግለህ ነፃ ካላወጣህ፤ ነፃ የሚያወጣህ ሌላ ኃይል የለም። ስለዚህ ያለመስዋዕትነት ነጻነት የለም። በተግባር ሲታይ ከውጭ ያለው አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ለትግሉ መንሲኤ ረዳት ኃይል እንጂ አንቀሳቃሽ ሞተር መሆን አይችልም። የእኛ ድክመት የወያኔ ጥንካሬ በመሆኑ ለወያኔ ሃያ አንድ ዓመት መንገሥ አስተዋጽኦ አድርገናል። ከወያኔ የተረፈን ነገር ቢኖር ክልላዊነት፣ ዘረኝነት፣ መናናቅ፣ እራብ፣ ውሸትና ጎሳ ለጎሳ እንደ ጠላት መተያየትን ብቻ ሳይሆን ጨርሶም ኢትዮጵያዊነትን ማጥፋት ነው። አብዛኞቻችን የፕሮፓጋንዳ እኩልነት/ልዩነት ጠባቡን የዘር ካባ አጥልቀን በመጓዛችን ምክንያት ወያኔ የሚያራምደውን የከፋፍለህ ግዛና የዘረኝነት ፖለቲካን ለመዋጋትና በአንድነትም ለመቆም ትልቅ ችግር ፈጥሮብናል።  ወያኔ ደካማ ጎናችንን ነጥሎ በመጠቀም ኢትዮጵያዊነት፣ የኢትዮጵያውያን   አንድነትና ትስስር ጉዳዮችን በአነሳን አጋጣሚዎች ሁሉ፤ መከፋፈያ ጽንሰ ሐሳባቸው የሆነው “የወደቀውን ሥርዓት ለመመለስ የሚታገሉ ደርጎች” ፣ትምክተኛ የአማራ ርዝራዦች፣ ጠባብ ኦሮሞዎች፣ ጥገኛ ደቡቦች  ወዘተ እያለና ያለፈው የኢትዮጵያ ሥርዓት በሙሉ የአማራ ሥርዓተ ጭቆና ዘመን  እንደነበረ ታሪክን በርዘው እያስተማሩና የኢትዮጵያን መልከ ምድር ቀደው በፈለጉት ዓይነት ለጥጠው እየሰፉት ናቸው። ለምሳሌ የትግራይን ገጸ ምድር የቀድሞውንና የአሁኑን ማመሳከር ቢቻል፡ አዋሳኝ የሆኑ የጎንደር፣ የወሎና የአፋር ክልሎች ለምን እንደጠበቡና የትግራይ ገጸ ምድር ለምን እንደተለጠጠ ማገናዘቡ ጥሩ ነው።

ኢትዮጵያን ቅኝ ለመግዛት የግድ ፈረንጅ ከባሕር ማዶ መምጣት የለበትም። አንድ ጎሳ በመሳሪያ አፈሙዝ አንበርክኮ ከገዛና የራሱን ጎሳ የበላይነትን የሚያንሰራራ፣ የሌላውን ዜጋ ዲሞክራሲያዊ መብት አፍኖ የሚይዝ፣ መዋቅረ መንግሥቱ ማለት መከላከያው፣ የፍትሕ፣ ሕግ አውጭና ሕግ ተርጓሚው ተቋማትንና የአገሪቷን ሐብትና ንብረት የራሱ አድርጎ እስከ በዘበዘ ድረስ ከቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ምንም ልዩነት የለውም። ኢትዮጵያ በወያኔ አገዛዝ ሥር ከወደቀች ከሃያ ዓመት በላይ የቆጠርን ብንሆንም፤ የወያኔ ሥርዓት ጥላቻና ሚዛናዊነት የጎደለው ሥርዓት ለመሆኑ በግልጽ እያየን ነው። ከአፈና፣ ከግድያ፣ ከስብእና ቀውስና ከሕልውና ሰለባ አልፎም የኢትዮጵያ ንብረት በሙሉ በትግራይ ወያኔዎችና በጥቅም ሆነ በጋብቻ ከትግራይ ዘር በተሳሰሩ ሰዎች ቁጥጥር ሥር ነው። የኢትዮጵያ የቴክኖሎጂ ማዕከል ትግራይ ናት። በኢትዮጵያ ጥራት ያለው ዩኒቨርስቲና የትምሕርት አሰጣጥ ማዕከል ትግራይ ነው። የኢትዮጵያ አየር ኃይል የጦሩ እዝና መሣሪያ ክምችት በትግራይ ነው። የባቡር መሥመር ሊዘረጋ ቢታቀድ ወደ ትግራይ ነው። አዲስ ፋብሪካ ቢቋቋም በትግራይ ነው። ከውጭ አገር መንግሥታት ከተሞች በክልል ደረጃ የግል ግኑኝነት ያላት መቀሌ ናት፡፡ ለትግራይ ክልል ብቻ የሚደረግ ሚዛናዊነት የጎደልውን አድሎን መዘርዘር ከፈለግን ጊዜም አይበቃንም። ሆኖም ይህ ሲባል ትግራይ ለምን ለማች ወይም አደገች ለማለት ሳይሆን ሁሉን አቀፍ መሠረተ ልማት የሚዘረጋ አስተዳደር፣ የጎሊና ዳኝነትና ሚዛናዊነት ለምን ጠፋ በማለት ነው። ከድሮም በተፈጥሮ ደረቅ የነበረው የትግራይ ክልል ዛሬ የመሥኖ ውኃ በቴክኖሎጂ ወጥቶለት አረንጓዴ ለብሶ የዳቦ ቅርጫት በመሆኑዋና ከእራብ በመላቀቋ ለዓለም ምሳሌነት ለፊሊም በሙብቃቷ እጅግ የሚያስደስት ሲሆን የተቀሩት የኢትዮጵያ ክልሎች በተፈጥሮ ለምለምና የበርካታ ወንዞችና ጅረቶች ተፈጥሯዊ ባለቤት ሆነው በአስተዳደር ጉድለት ብቻ ዛሬ ለድርቅ ለእራብና ለቸነፈር ለሞትና ለእልቂት መዳረጋቸው በጣም ያሳዝናል። ይህም የትግራይ ወያኔ ቅኝ ገዥነቱን ያረጋግጥልናል።

የመቀሌ ለሁሉም አማካይ ከሆነችው ከአዲስ አበባ በልጣ የጋራ ንብረትና የኃይል ክምችት መሆኗ ወያኔ ለትግራይ የበላይነት ኢትዮጵያን እያደማ እንዳለ በግልጽ ይታይበታል። ለሁላችን ግልጽ መሆን ያለበት አንዱ ክልል ከሌላው የሚበላለጠው እግዚአብሔር ባደለው የተፈጥሮ ሐብቱ ብቻ ነው። የልማት ፈሰስ ሚዛናዊነቱን ይጠበቅ እንላለን። ትግራይ ክልል በጅምላ ለምን ይወሳል? የሚሉ አድር ባዮች በሁሉም አቅጣጫ ቢኖሩም፤ በአፋችን የጥጃ ሥጋ የጎረስን ይመስል እንደ ሙጫ አጣብቆን ዝም ከማለቱ በግልጽ መነጋገሩ ያንዣበበብንን አደጋን ሊያቀልልን ይችላል ብዬ አስባለሁ። ብልጣብልጡ ወያኔ በከፋፋይነት ወንጀል ስለሚፈርጃቸው አድርባይ ፖለቲከኞች ትግራይ የሚል ቃላትን በፖለቲካው ውስጥ መተንፈስን በጣም ይፈራሉ። በዚህ አጋጣሚ ከትግራይ የተወለድክና የተጋባህም ሁሉ ከጎጤኝነት ኢትዮጵያዊነት እንደምበልጥ አውቀህ አንድነታችን እንዳይናጋ ሐላፊነት ይጠበቅብሃል፤ ጠባብነትን እንዋጋ ማለት የኢትዮጵያ አካል የሆነቿውን ትግራይን ጥላቻ እንዳልሆነ መታወቅ አለበት። ወያኔነት ከትግራይ ምድር የበቀለ ዘረኝነት ስለሆነ፤ ሁሉም ወያኔ ትግራይ ነው። ነገር ግን ሁሉም የትግራይ ተወላጅ ወያኔ አይደለም።

አንድ አባት እያለን የት አለን? ይላሉ።

ታሪክ አስክደን፤
ባሕልን አጥፍተን፤
ባዳነትን ክበን፤
ጀግንነትን ረግመን፤
እየሳቅን አልቅሰን፤
እየኖርን ሞተን
እያለን የት አለን?
ረሐብን ጠግበን፤
ጥማትን ረክተን፤
እርዛትን ሞቀን፤
እየኖርን ሞተን
እያለን የት አለን?

ጽጌ መዓዛን አግማምተን፤
ውብት ደም ግባትን ተጠይፈን፤
ጥራት ንፅሕናን አብክተን፤
የላብ ጠረን ቁናሰን ጎምጅተን፤
በሳቅ ሐዘን ቁዘማ፤
ልባችን እየደማ፤
የነገርን ሁሉ መልክ፤
ገለባብጠን ያለ ልክ፤
በፈርሱ አረግነው ልክክ፤
በጨዋታ ዝምታ፤
ቆም ብለን ለአንዳፋታ፤
ምን ብለን ምን እንበል፤
ገዝፈን! ገዝፈን! ስንቀል።

አንድነታችን ለዘለዓለም ይኑር።

ደመላሽ ካሣ

ካሊፎርኒያ።